"ሌ\ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም በፍቃዳቸው ለፍርድ ለመቅረብ ዝግጁ ናቸው..."

ብ\ጄ ታመነ ድልነሳው የኮ\ሉ የቅርብ ወዳጅ





ብርጋዴር ጄነራል ታመነ ድል ነሳው ይባላሉ ፡፡በቀዳማዊ ሃይለስላሴ መንግስት እና በዘመን ደርግ ከሰላሳ አመታት በላይ በተለያዩ ወታደራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ሃላፊነቶች ላይ በከፍተኛ አመራር አገራቸውን አገልግለዋል፡፡ በተለይ ደግሞ በዘመነ ደርግ በቀድሞዋ ሩሲያ የኢትዮጵያ ወታደራዊ አታሺ፣ በስተመጨረሻም በእስራእል የኢትዮጵያ ባለሙሉ አምባሳድር በመሆን እስከ ደርግ ውድቅት ድረስ ሰርተዋል፡፡ ኮ\ል መንግስቱ ከስልጣን በወረዱ ማግስት በስደት ከሚገኙበት ዙምባብዌ (ሃራሪ) ስልክ በመደወል ስለአነጋጋሪው የኮ\ሉ ከአገር የአወጣጣቸው ምስጤር ካካፈሏቸው ጥቂት የቀድሞ መንግስት ባለስልጣናት መካከል አንዱ ናቸው ፡፡ብ\ጄ ታመነ በምድረ አሜሪካ በላስቬጋስ ከተማ ከሚሰራጨው ህብር ራዲዮ ጋር በቅርቡ ባደረጉት ሰፊ ቃለ ምልልስ ኮ\ል መንግስቱ እራሳቸውን ለፍርድ ለማቅርብ ስለማሰባቸው፣ ስለ የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ እንዲሁም ስለወደፊቱ የኮ\ል መንግስቱ እጣ ፍንታ የራሳቸውን ግምት ሰንዝረዋል፡፡ ከኮሎኔል መንግስቱ ጋር ከመስመራዊ መኮንነት አንስቶ እስከ አሁን ድርስ የቅርብ ግንኙነት እንዳላቸው የሚናገሩት ብጄ\ል ታመነ ከቀድሞው የኢትዮጵያ ርዕሰ ብሄር ጋር ያሳለፉቸው ብዙ ትዝታዎችን ጨምሮ በአገር ጉዳይ ፣በግል ኑሮአቸው እና በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዩች ዙሪያ ከራዲዮው የምእራብ አውሮፓ ዘጋቢ ታምሩ ገዳ ጋር ካደረጉት ሰፊ ቃለምልልስ መካከል ከፊሉ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ መልካም ንባብ ይሁንልዎ፡፡

ጥያቄ:- ውትድርና በንጉሱ እና በዘመነ ደርግ ምን ይመስል ነበር?

ብ\ጄ ታመነ:- ደርግ ወደ ስልጣን ሲወጣ ልምድ እና እውቀት የነበራቸውን የቀድሞ ሰራዊትን በማቀፉ ምክንያት በሁለቱም ስርአት የጎላ ልዩነት አልነበረውም፡፡ በንጉሱ ዝምን ቃለመሃላ ሲፈጸም "ለአገሬ እና ለንጉስ ነገስቴ ታማኝ ነኝ" ይላል ፡፡በደርግ ደግሞ "ለአገሬ እና ለሰንደቅ አላማዮ" ይላል፡በሁለቱም ዘመን ሃይማኖት የግል ነው፡፡ ዘር የሚባል ነገር ጨርሶ አይታወቅም፡፡

ጥያቄ:- በአሁኑ ወቅት በስልጣን ላይ ያሉት የኢሃዴግ ከፍተኛ መኮንኖች አብዛኞቹ የአንድ ብሄር ልጆች ናቸው ይባላል ፡፡ስለዚህ አወቃቀር አውንታዊ እና አሉታዊ ጠቀሜታ የሚሉት ነገር ካለ?

ብ\ጄ ታመነ:- በእውነቱ ይሄ የሚባለው ነገር ለማውራት እንኳን በጣም አሳፋሪ ነው ፡፡ምክንያቱም በንጉሱ ዘመን ሆነ በደርግ ስርአት በአገሪቱ ሃብት በአገር ውስጥ እና በባህር ማዶ ወታደራዊ እውቀት ያካበቱ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ለፖለቲካ ፍጀታ ሲባል ተባርረው ወይም ከአገር እንዲሰደዱ ተደርገው በምትካቸው የወታደራዊ ሳይንስ እውቀት የሌላቸው የአንድ በሄር ልጆችን ብቻ

ማስባስብ ትልቅ ስህተት ነው፡፡አንዳንድ መረጃዎች እንደሚሉት ከሆነ ወደ ስልሳ ሁለት(62) ከሜገመቱት ከፍተኛ መኮንኖች ውስጥ ስልሳ አንዱ(61) የትግራይ ብሄር ተወላጆች ናቸው፡፡እዚያ ውስጥ አንድ(1) የአማራ ብሄር ተወላጅ ለይስሙላ እንዳለ ይነገራል፡፡ አንድ ሰራዊትን በዘር እንዲከፋፈል ከተደረገ የወደፊት አደጋው ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

ጥያቄ:- የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዘነዳንት ኮ\ል መንግስቱን በቅርብ ያውቋቸዋል ይባላል ፡፡ እውቀታችሁ እስከ ምን ድረስ ነው?

ብ\ጀ ታመነ:- ኮ\ሌ መንግስቱን የማውቃቸው ገና የም\መቶ አለቃ ከሆንበት ጊዜ አንስቶ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን የቅርብ ወዳጆች ነን ፡፡

ጥያቄ:- ታዴያ ዛሬስ ኮ\ል መንግስቱን ያገኙዋቸዋል? ምን ያህል ጊዜ ትገናኛላችሁ?

ብ\ጀ ታመነ:- ብዙ ጊዜ አገኛቸዋለሁ፡፡አስፈላጊ ከሆነ ስልክ እደውልላቸዋለሁ፡፡ እርሳቸውም እንዲሁ ይደውሉልኛል ፡፡

ጥያቄ:- ኮ\ል መንግስቱ ቁጡ እና አማባገነን መሪ ናቸው ይባላል፡፡ በዚህ ዙሪያ የሚሉት ካሎት?
ብ\ጀ ታመነ :-ስልጣን ላይ እስከ ወጡ ድረስ ይህን አይነት ጠበይ አላየሁባቸውም ፡፡ ነገር ግን ወደ ስላጣን ከወጡ በሁዋላ ይሄ የሚባለውን ሁሉ እሰማለሁ ፡፡እኔ ግን በስፍራው ተገኝቼ ያየሁት ነገር የለም፡፡

ጥያቄ:- ስለ ኮ\ል መንግስቱ ከአገር አወጣጥ ብዙ ይወራል፡፡ ገሚሱ ሰራዊቱን እና ህዝቡን ጥለውት ኮበለሉ ሲል አንዳንዱ ደግሞ በተንኮል እና በሴራ ነው የወጡት... ወዘተ ይላል፡፡

ብ\ጀ ታመነ:- እኔ ዲቴይል (ጥልቅ) የሆነ መረጃ የለኝም ነገር ግን እርሳቸው ከአገር ሲወጡ እኔ በእስራኤል አምባሳደር ነበርኩኝ፡፡ በሁዋላ እንደሰማሁት ከሆነ ግን እርሳቸው ናይሮቢ በደርሱ ጊዜ በስልክ ሊያነጋግሩኝ ፈልገውኝ ሳንገናኝ ቀረ ፡፡ነገር ሳነገናኝ ቀረን ፡፡አንድ የእስራኤል ታዋቂ ጋዜጣ "ኮ\ል መንግስቱ የቅርብ ወዳጃቸው የሁኑት አምባሳደር ታመነን ፈልገዋቸው አጧቸው...ወዘተ " ብሎ በጊዜው ዘግቧል ፡፡በበነጋታው ዙምባብዌ ( ሐራሪ ) እንደደረሱ ስልክ ደውለውልኝ ስለአዋጣጣቸው በሴራ እና በተንኮል እንደወጡ ነው አስተያየታቸውን የስጡኝ፡፡ከዚህ ያለፈ ብዙ የማውቀው ነገር የለም፡፡

ጥያቄ:- ኮ\ል መንግስቱ "ዘወትር የኢትዮጵያ ህዝብ ይፍረደኝ..." ይላሉ ስለሜባለውስ?

ብ\ጀ ታመነ:- አዎ አሁንም ቢሆን እንደዚያ ይላሉ ፡፡የፍርዱን ጉዳይ በተመለከተ እኔን የሚፈርደኝ ወያኔ( ኢህአዴግ ) አይደለም፡፡ የሚፈርደኝ ህዝቡ ነው ባይ ናቸው ፡፡ወደፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጠው መንግስት ስልጣን ሲይዝ እራስቸው በማንኛውም ሰዐት ወደ አገር ቤት መጥተው ፍርዳቸውን ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን ብዙ ጊዜ ይናገራሉ፡፡ለዚህ አባባላቸው ምንም አይነት ጥርጣሬ የለውም፡፡ ለነገሩ እኛም ብንሆን እኮ ይህንን ሁሉ አመት ስናገለግል በሙሉ ፐርፌክት (ፍጹም) ነበርን አንልም፡ ፡የህዝብ መንግስት ሲመጣ ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን ፡፡እርሳቸውም ቢሆኑ መሪ ስለነበሩ ተጠያቂ ለምሆናቸው የሚያምኑበት ይመስለኛል፡፡

ጥያቄ:- በኮ\ል መንግስቱ ታሪክ ዙሪያ አንድ አዲስ መጽሀፍ በገበያ ላይ ወጥቷል ይባላል ፡፡ስለዚህ ጉዳይ ከኮ\ል መንግስቱ ጋር ተወያይታችሁ ታውቃላችሁ?

ብ\ጀ ታመነ :-እኔ እስከ አሁን ድረስ የማውቀው አንዴት ጋዜጣኛ ጻፈችው የተባለውን ብቻ ነው፡፡ሌቀመንበር መንግስቱን አሁንም እይጠየቅኳቸው ነው፡፡ አንድ ፣ሁለት ወይም ሶስት ቮሌዩም የሜደርስ መጽሕፍ ማዘጋጀታቸውን ነግረውኛል፡፡ ይህ መጽሕፍ በቅርቡ በገበያ ላይ ይውላል ብይ እገምታሉ፡፡መጽሐፉ ለመጪው ትውልድ ትምህርት ስጪ ይሆናል የሜል አስተሳሰብ አላቸው፡፡

ጥያቄ:- ኮ\ል መንግስቱ ስለ ኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?

ብ\ጄ ታመነ :-በእውነቱ ከሆነ አሁንም ሳንጋግራችው ልክ እዚያ የድሮ ስልጣን ላይ እንዳሉ አይነት ነው አነጋገራቸው ፡፡በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በጣም ጥልቅ የሆነ መረጃ እና አመለካከት እንዳላቸው ተገንዝቤያለሁ ፡፡አንዳንድ ጊዜ ወቅታዊ ጽሁፎችን (መጻሕፍት) ይፈልጋሉ ወይ ብዮ ስጠይቃቸው ምንም አይነት መጽሃፍ እንደማይፈልጉ እና ቀድሞ እንደደረሳቸው ነው የሜነግሩኝ፡፡ ከዚህ እና መሰል ውይይቶቻችን አኳያ ስለ አገሪቱ ሁኔታ በቅርቡ የሚከታተሉ ይመስለኛል፡፡

ጥያቄ:- ኮ\ል መንግስቱ በሁሉም ሙያ ውስጥ ባለሙያው እኔ ብቻ ነኝ ይላሉ በማለት የሜያሚቸው ወገኖች አሉ?

ብ\ጄ ታመነ:- እኔ እስከማውቃቸው ድርስ "ባለሙያው ይናገር" የሚሉ ስው ናቸው ፡፡ትዝ ይለኛል በአንድ ወቅት አብዮቱ እንደፈነዳ ሰሞን በቡና ዋጋ ለውጥ የተነሳ "አይፋ "የተባለ መኪና ከ ቀድሞዋ ምስራቅ ጀርመን ለመግዛት ታስቦ የደርግ ባለስልጣናት ስለመኪናው ግዤ አስተያየት እንዲሰጡ ተጠይቀው ነበር ፡፡ ኮ\ል መንግስቱ ያንን ሃሳብ በመቃወም በምትኩ በጊዜው የነበሩ አቶ ጌታችው የሚባሉ ባለሙያ አሰተያየት እንዲስጡበት አበክረው በመጠየቃቸው ያ መኪና አቶ ጌታቸው ባቀረቡት ሙያዊ አስተያየት መሰረት እንዲገዛ መደረጉን አስታውሳለሁ ፡፡ ወደ መጨረሻ አካባቤ እንደምስማው ግን ሁሉንም ነገር ከእኔ ውጩ ለአሳር ነው ይላሉ የሚል ወቀሳ እንደነበረባቸው ሰምቼአልሁ፡፡ይሄም ቢሆን እኮ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው እርሳቸው ብቻ ሳይሁኑ ከእርሳቸው ስር ያሉ ባልስልጣናትም ቢሆኑ ተጠያቂዎች ናቸው ፡፡ ለምሳሌ ያህል ህክምናን በሚመለከት ሃኪሙ ባለሙያው እኔ ነኝ ቢላቸው፣ በግብርናውም ፣በንግዱም ዘርፍ እንዲሁ ቢሏቸው ምናልባት ሊሰሙ ወይም ሊመለሱ ይችሉ ይሁናል፡፡በውትድርናውም ቢሆን እርሳቸው መጽሃፍ እንብበው ካልሁነ በቀር ሙሉ በሙሉ የእግረኛ አዛዥ አልነበሩም፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ አንዳንድ ሰዎች ናቸው ስልጣናቸውን መከታ አድርገው ወደዚያ እንዲገቡ የሚገፋፉዋቸው፡፡

ጥያቄ:- እንዳንድ ሰዎች ሲሉ ከስራቸው ያሉ ባልስልጣናት ለማለት ፈልገው ነው?

ብ\ጄ ታመነ:- አዎ ኮ\ል መንግስቱ ስህተትም ቢሰሩ ጓድ ሊቀመንበር እርሶ ትክክል ኖት የሚሉ በርካታ ባልስልጣናት እንደ ነበሩ ትዝ ይለኛል ፡፡ይሄንን ጉዳይ ከ አንዴም ሁለቴ በአይኔ አይቻለሁ፡፡ ስማቸውን ልጠቅስ የማልፈልገው በስልጣን ላይ የነበሩ ሁለት ስዎች (አሁን በህይወት የሉም) ኮ\ል መንግስቱ ያልሁነ ነገር ሲናገሩ እነዚህ ባልስላጣናት ሲናገሩ "በጓድ ሊ\መንበር ንግግር ላይ በማከል... ወዘተ" እያሉ እንጂ "የጓድ ሊ\መንበር ንግግር ትክክል አይደለም...ወዘተ" ሲሉ አልስማሁም፡፡ ምንም እንኳን ነገሩ ያለፈ ቢሁንም ሳስበው በጣም ያሳዝናኛል፡፡

ጥያቄ:- ኮ\ል መንግስቱ የሕዝብ ንብረት እና ገንዝብ አሸሽተዋል ስለሚባለውስ ምን ያህል ያውቃሉ?

ብ\ጄ ታመነ:- በእውነቱ እኔ የማውቀው ነገር የለም፡፡ ግማሹ አሸሽተዋል ሲል በወሬ ደረጃ እንስማልን ግን በጊዜው እርሳቸውን በቅርቡ የሚያውቁ የአንድ ባለስልጣን ሚስት ወደ እየሩሳሌም ሲመጡ አግኝቻቸው ነበር ፡፡ የተባለው ነገር እንዴት ነው ብዮ ጠይቄያቸው ነበር፡፡ እርሳቸውም "የመንግስቱ አገዛዝ ባለቤቱን አስሯል፣ደብድቦም በስተመጨረሻ ገድለውታል ፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ በደል ቢፈጸምብኝም እንዲያው በደፈናው መንግስቱ እንዲህ ናቸው አልልም ፡፡ይሄ ኮ\ሉ ንብረት ዘርፈዋል ስለሚባለው ነገር ጨርሶ ወሬ እና አሉ ባልታ ...ወዘተ ነው "ብለው ነግረውኛል ፡፡ከዚህ ውጩ ብዙ የማውቀው ነገር የለም፡፡

ጥያቄ:- እርሶ ለሁለት መንግስታት አገልግለዋል፡፡ ታዴያ ለንጉሱ እና ለደርግ መንግስት ዋንኛ የውድቀት መንስኤ ምን ነበር ይላሉ?

ብ\ጄ ታመነ:- ንጉሱም ሆኑ ኮ\ል መንግስቱ መሻሻል በሜገባው ጉዳይ ዙሪያ አፋጣኝ እርምጃ ያለመውሰዳቸው ለውድቀታቸው ምክንያት ይመስለኛል፡፡እኔ እስከ ሜገባኝ ድረሰ አንድ መሪ ሰጥቶ መቀበል የሚያውቅ መሆን አለበት፡፡ እርሱ ትእዛዝ ይሰጣል ትእዛዙ የተከበረ ነው ፡፡ በምላሹም መቀበልን ማውቅ አለበት፡፡ሰጥቶ መቀበልን ትቶ እርሱ ሰጩ ብቻ ከሆነ እርሱ

አምባገነን ነው ፡፡ መቀበልን ብቻ የሚጠብቅ ከሆነ እርሱም ቢሆን አደርባይ ነው፡፡ በሁለቱ አገዛዝ ሰጥቶ መቀበል የሚለው ፍልስፍና አልነበርም፡፡

ጥያቄ:- ኮ\ል መንግስቱ ብዙ ጊዜ ለምን አሜሪካንን አምርረው ይጠላሉ?

ብ\ጀ ታመነ:- እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሁለታችንም በአሜሪካው የአባርዴን ወታደርዊ ኮሌጅ ውስጥ አብርን ነበር የተማርነው፡፡ ማሰልጠኛው በጣም ትልቅ እና ዘመናዊ ተቋም ቢሆንም በጊዜው በውስጡ ምንም አይነት የመዝናኛ ስፍራ ባለመኖሩ በአካባቢው ወደ ነበረ አንድ ትንሽ የመዝናኛ ስፍራ ጎራ እንላለን ፡፡ ያቺ በጥራት እና በይዘቷ መርካቶ ውስጥ ካሉ የሻይ ቤቶች የምታንስ ሬስቶራንት የመግቢያ በር ላይ አንድ እንዲህ የሚነበብ ጽሁፍ አለ "ውሻ እና ጥቁር በኋሮ በር!" ይላል ፡፡ በእኛ እና በአሜሪካኖች መካከል የርዕዮት አለም ልዩነት እንዳለ ሆኖ ያቺ የዘረኝነት ጽሁፍ የሁላችንንም ስሜት ብዙ ጊዜ ነክታለች ፡፡ ሊቀመንበር መንግስቱ ከአሜሪካ ከተመለሱ በሁዋላም ቢሆን ያቺን የዘረኛ ጽሁፍን ዘውትር በንዴት ያነሱዋት ነበር ፡፡

ጥያቄ:- የኮ\ል መንግስቱ የወደፊት እጣ ፈንታ ምን ይሆናል ብለው ይገምታሉ?

ብ\ጀ ታመነ:- የወደፊት እጣፈንታቸው እንዲህ ይሆናል ብሎ መገመት ይከብደኛል፡፡እድሜያቸው እየገፋ ሄዷል፡፡ መጽሃፋቸውን ከጻፉ በሁዋላ ወደፊት የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱ መንግስት ሲያቋቁም አገር ቤት ገብተው የሚጠበቅባቸውን ፍርድ ይሁን ቅጣት ሊቀበሉ ወይም ትምህርትም ከሆነ ሊሰጡ ይችላሉ ፡፡ከዚያ ውጩ ግን ከዙምባብዌ ወጥተው ወደ ሌላ አገር ሄድው ይኖራሉ ብዮ አልገምትም ፡፡ ከዚህ በሁዋላ ወደ ሌላ አገር ዳግም መሰደድ የእርሳቸው ፍላጎት የሚሆን አይመስለኝም፡፡

ጥያቄ:- በስተመጨረሻ ለአድማጮቻችን የሚያስተላልፉት መልእክት ካሎት?

ብ\ጀ ታመነ:- ሁላችንም ለአገራችን ይበጃል ያልነውን ሰርተናል፡፡ ይሄ የንጉሱ ፣ይሄ የደርግ ወይም ይሄ የወያኔ ወገን ነው እየተባባልን መነቋቆሩ ለአገራችን እና ለሕዝባችን ብዙም አይጠቅምም ፡፡ከዜህ አይነቱ ጠባብ አመለካከት ወጥተን በአንድነት እና በመከባበር አገራችን ከልመና እን ከድህነት የምትላቀቅበትን መንገድ መቀየሱ የተሻለ ነው እላልሁ፡፡

ጥያቄ:- ጄነራል ስለጊዜዎት በአድማጮቻችን ስም በጣም አመሰግናለሁ ፡፡
ብ\ጀ ታመነ :- እኔም ስለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ፡፡